# የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት በማህበረሰቡ ውስጥ

ከውጭ መንግስታት ዛቻና ማስፈራሪያ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል

**እውነታዊ ጽሁፍ ወረቀት** / March 2023

afp.gov.au

## መግቢያ

የውጭ ጣልቃ ገብነት በአውስትራልያ ህዝብ፣ ሉአላዊነት ና ደህንነት እንዲሁም በብሄራዊ ተቋማችን ንጽህና ላይ ከባድ ስጋትን ያመላክታል። የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት ስጋት በአንድ የአውስትራሊያ ማህበረሰብ ክፍል ላይ አይገደብም ወይም በአንድ አገር-መንግሥት አይፈጸምም። ጠላት የውጭ ሀገር ተዋናዮች (በሌሎች ሀገራት ላይ የጥላቻ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሃገራት) በሁሉም የመንግስት ደረጃ እና በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ የአውስትራልያ ውሳኔ አስፈጻሚዎችን ለማደናቀፍ የሚያስችሉ እድሎችን እየፈጠሩ እና እየተከታተሉ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል - ዲሞክራሲያዊ ተቋማት፤ ትምህርትና ምርምር ጥናት፤ መገናኛ ብዙሃን እና መገናኛ ዘዴዎች፤ ወሳኝ መሰረተ ልማት፤ እና ከሁሉም በላይ የባህል እና የቋንቋ ልዩነት (CALD) ማህበረሰቦቻችን ያቀፈ ነው።

## የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት በማህበረሰቡ ውስጥ

በማህበረሰቡ ውስጥ የውጭ ጣልቃ ገብነት በአውስትራሊያ የበርካታ ባህሎች አኗኗር ላይ ጉዳት እና ተፅዕኖ ለማሳመር ሲባል በውጭ መንግስታት የሚመራ፣ የሚቆጣጠር ወይም በገንዘብ የተደገፈ እና በCALD ማህበረሰቦች ላይ ያነጣጠረ ዛቻ እና ማስፈራሪያ የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል። የውጭ መንግሥታት ለተለያዩ ዓላማዎች በማህበረሰቦች ውስጥ ጣልቃ ሊገቡ የሚችሉት:

- በውጭ አገር መንግስት የውስጥና የውጭ ፖሊሲዎች ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችን ዝም ለማሰኘት
- የCALD ቡድኖች አባላትን እንቅስቃሴ (በኦፍላይን እና በኢንተርኔት) ለመከታተል
- የውጭ አገር መንግስትን አመለካከትና ፖሊሲ ለማራመድ
- ለውጭ መንግስት ጥቅም ሲባል መረጃ ለማግኘት
- በሰፋፊው ህዝብ አመለካከትና አስተያየት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ነው።

## በማህበረሰቡ ውስጥ የውጭ ጣልቃ ገብነት ብዙ መልክ ሊኖረው ይችላል

በዚህ የሚካተት:

- ጥቃት ወይም ዛቻ
- ማሰቃያ
- አፍኖ መውሰድ፣ ህገ ወጥ እስር ወይም ነጻነትን መንፈግ
- መከታተል እና የማይፈለጉ አካላዊ ወይም ኤሌክትሮኒክ ክትትል
- አንድ ግለሰብ በውጭ አገር ያሉ ቤተሰቦቻቸውን ወይም ግብረ አበሮቻቸውን በማስፈራራት እንዲፈጽሙ ማስገደድ

- የአንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ለማዋረድ በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ኢንተርኔት ላይ የተዛቡ የመረጃ ዘመቻዎችን ያካሄዳሉ።

በ1995 (Cth) አንቀጽ ህግ መሠረት የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት ለመመስረት እንቅስቃሴው ከውጭ መንግሥት ወይም ከውክልናው ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። በተጨማሪም ህግ አስከባሪ ድርጅቶች ወንጀልን በሚገመግሙበት ጊዜ በአውስትራሊያ አስተዳደር ግዛት ወይም በተሪቶርይ ክልል ውስጥ የሚፈጽሙ ወንጀሎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላሉ።

## የጥቃት ዒላማ የሆኑት እነማን ናቸው?

የውጭ አገር መንግሥታት ዒላማ ሊሆኑ የሚችሉት:

- በአውስትራልያ የሚኖሩ የቀድሞ ወይም የአሁኑ ዜጎች
- የፖለቲካና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች
- ተቃዋሚዎች
- ጋዜጠኞች
- የፖለቲካ ተቃዋሚዎች
- የሃይማኖት ወይም የአናሳ ጎሳ ቡድኖች።

## እርዳታ ለመስጠት ምን ማድረግ እችላለሁ?

በማህበረሰቡ ውስጥ የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት ሪፖርቶች በሙሉ ግልጽ የሆነ የአውስትራሊያ ፌደራል ፖሊስ AFP ምላሽ የሚፈጥሩ ባይሆኑም እያንዳንዱ ሪፖርት ግን እየታዩ ያሉትብ ድንገተኛ ችግሮችን ለይቶ ለማወቅ **ስዕል ለመገንባት ይረዳል**።

በማህበረሰቡ ውስጥ የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት ማንኛውም ጉዳይ እና/ወይም አጋጣሚዎች **ለብሔራዊ ደህንነት ሆትላይን (NSH)** ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

- NSH በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን የሚሰራ ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት ሊከሰት ስለሚችል ስጋት ሪፖርት ለማድረግ ማእከላዊ የግንኙነት ቦታ ነው።
- NSH ኦፕሬተሮች እርስዎ በሚሰጡት መረጃ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ እናም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለማጣራት ወደ ህግ አስከባሪዎች እና ደህንነት ድርጅቶች ያስተላልፋሉ.
- NSH ኦፕሬተሮች እያንዳንዱን ስልክ ጥሪ በቁም ነገር ይይዟል እንዲሁም የተቀበሉት መረጃዎች በሙሉ ከፍ ያለ ዋጋ ግምት ይሰጣል።
- አሳሳቢ ጉዳይ ሪፖርት ማድረግ ትልቅ እርምጃ ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን። የግል ሚስጥር የመጠበቅ መብትህን በቁም ነገር እንመለከተዋለን። ስማችሁ ሳይታወቅ መቀጠል ከፈለጋችሁ እባካችሁ ለኦፕሬተሩ ንገሩት።
- በመረጃው ጥንቃቄ የተሞላበት ባህርይ ምክንያት በስልክ ጥሪዎ ወይም በኢሜልዎ ውጤት ላይ ምክር አይሰጥዎም።

የሚያቀርቡት መረጃ ለAFP በማህበረሰቡ ውስጥ የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር ለመርዳት የሚያስፈልገው የጎደለው ነገር ሊሆን ይችላል።

**NSH**’ን ማነጋገር የሚቻልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ:

- **በቁጥር መደወል: 1800 123 400**
  - ከአውስትራሊያ ውጭ ሆኖ ለመደወል: (+61) 1300 123 401
  - ለ TTY ተጠቃሚዎች (የመስማት ችግር ላለበት ተጠቃሚዎች): 1800 234 889
  - **አስተርጓሚ ከፈለጉ፤ እባክዎለትርጉምና አስተርጓሚ አገልግሎት በቁጥር 131 450 መደወል እና ከአገር አቀፍ ደህንነት ሆትላይን መስመር እንዲያገናኝዎ ምወጠየቅ**
- **ተክስት/SMS**
  - እባክዎ ያለዎትን መረጃ በተክስት መልእክት በቁጥር 0429 771 822 አድርጎ መላክ
- **ኢሜል**
  - እባክዎ ያለዎትን መረጃ በኢሜል: hotline@nationalsecurity.gov.au አድርጎ መላክ
- **ፖስታ:**
  - እባክዎ ያለዎትን መረጃ ለሚከተለው አድራሻ በፖስታ መላክ:

    National Security Hotline
    Department of Home Affairs
    PO Box 25
    Belconnen ACT 2616

## ሪፖርት ማድረግ የሚቻልባቸው ሌሎች መንገዶች

በተጨማሪም የሚያሳስብዎትን ነገር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በተለያዩ ዘዴዎች ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

- በኦንላይን ኢንተርኔት ላይ ከባድ በደል ለተፈጸመባቸው ነገሮችን ለማስወገድ eSafety ይረዳል። በኢንተርኔት ላይ የሚፈጸመውን ከባድ ጥቃት በድረገጽ esafety.gov.au/report ላይ ለኢ-ሴፍቲ/eSafety ኮሚሽነር ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።
- በማንኛውም መንገድ ፍርሃት ወይም ስጋት ከተሰማዎ ማነጋገር የሚችሉት:
  - **ለፖሊስ- በወቅቱ ላለ ስጋር በ 000 መደወል**
  - **ፖሊስ - የሞት ስጋት ላልሆነ የተፈጠረ ፍራቻ ላልሆነ በስልክ 13 14 44 አድርጎ ፖሊስ እንዲገኝ መደወል።**
- ለኮመንወልዝ ወንጀል ለAFP በኮመንወልዝ ወንጀል ይዘት ድረገጽ forms.afp.gov.au/online_forms/report_a_crime አድርጎ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። የኮመንወልዝ ወንጀል ምን እንደሆነ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን በድረገጽ afp.gov.au/contact-us/report-commonwealth-crime#What-is-a-Commonwealth-crime ላይ ይመልከቱ።
- ማንኛውም የማህበረሰብ አባል ስለስለላ ወይም የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት እንቅስቃሴዎችን በቀጥታ ወደ AFP’s አባል (AFP የማህበረሰብ አገናኝ ቡድንን ጨምሮ) ጋር በመነጋገር ሪፖርት ማድረግ ይችላል።

## የውጭ አገር ጣልቃ ገብነት በማህበረሰቡ ውስጥ ሪፖርት በማድረግ ምን መጠበቅ እችላለሁ?

AFP በማህበረሰቡ ውስጥ ለውጭ አገር ጣልቃ ገብነት እያንዳንዱ ሪፖርት ማጣራት አይችልም። እያንዳንዱ ለNSH የሚደረግ ስልክ ጥሪ ወይም የወንጀል ሪፖርት በየደረጃው የሚገመገመው ማንኛውም የወንጀል ድርጊት ተለይቶ የሚታወቅ መሆኑን ለማወቅ ነው። ሪፖርት ማድረግ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:

- ጉዳዩ ፖሊስ እርምጃ እንዲወስድ የህግ መስፈርትን ስለማያሟላ ምላሽ ላይኖርበት ይችላል
- AFP ማጣራት ይችላል
- ሌላ የፖሊስ አገልግሎት ወይም የመንግስት ወኪል ጉዳዩን ሊይዘው ይችላል።

ከአውስትራሊያ ውጭ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች የፍርድ መስጫ ስልጣን ለመተግባር ገደብ ይኖረዋል።

## የዛቻ ማስፈራራት ዓይነቶች

### በአካል ዛቻ ቢሰነዘርብዎት

- ስጋቱን ልክ እንደ በቃል እንደተነገረው መጻፍ ወይም መመዝገብ።
- ስጋቱን ስለፈጠረው ሰው (ስም፣ ጾታ፣ ቁመት፣ ክብደት፣ የጸጉርና የዓይን ቀለም፣ ድምጽ፣ አለባበስ፣ ወይም ማንኛውም ሌላ መለያ ገጽታዎች)።
- ስጋቱን ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ።

### በስልክ ተደርጎ ዛቻ ፍርሃት ከደረብዎ

- የሚቻል ከሆነ በአቅራቢያዎ ያሉ ሰዎች እንዲያዳምጡና ለፖሊስ መረጃ እንዲሰጡዎ ምልክት ያስርጉላቸው።
- • ከተቻለ ስልክ ጥሪውን ይመዝግቡ።
- • የዛቻውን ትክክለኛ ቃላት መጻፍ።
- • ማንኛውንም መረጃ ከስልኩ የኤሌክትሮኒክ ስዕል ላይ ኮፒ ማድረግ።
- • ዝርዝር ጉዳዮችን ከፖሊስ ጋር ለመወያየት ዝግጁ መሆን።

### የጽሁፍ መልዕክት፣ የቀጥታ/የግል መልእክት፣ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ኢሜልን ጨምሮ በኤሌክትሮኒክ ስነ-ዘዴ አማካኝነት ስጋት ላይ ከወደቁ

- የተላኩ መልእክቶቹን አለመሰረዝ።
- የመልእክት መረጃውን (ርዕሰ ጉዳይ መስመር፣ ቀን፣ ሰዓት፣ ላኪ ወዘተ) ቅጂ፣ ፎቶግራፍ፣ ስክሪንሾፍ ወይም ኮፒ ማተም። ጊዜያዊ እንዲሆኑ ታስበው የተዘጋጁ መልእክቶችን ለማስቀመጥ ወይም ስክሪንሾት ለማድረግ ጥረት ማድረግ።
- ዛቻ ፍርሃት እንደደረሰብዎ ወዲያውኑ ለፖሊስ ማሳወቅ።
- ሁሉንም የኤሌክትሮኒክ ማስረጃዎች ማስቀመጥ ይሆናል።

**እራስዎን ከነዚህ አይነት ስጋቶች ለመከላከል የሚከተሉትን ምክሮች ይከተሉ:**

- ከማይታወቁ ላኪዎች የኤሌክትሮኒክ መልእክቶችን ወይም የያያዙትን አለመክፈት
- በማህበራዊ ድረ-ገጾች ላይ ከማይታወቁ ወይም ከማይጠይቁ ግለሰቦች ጋር አለመግባባት
- በመሳሪያዎችዎ/አካውንቶችዎ ላይ ያለዎት የደህንነት ማቀነባበሪያዎች ወደ ከፍተኛው የጥበቃ ደረጃ የተቀመጡ መሆናቸውን ያረጋግጡ
- የሳይበር ወንጀለኞች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችዎን ሊያዳክሙ እና የግል መረጃዎን ሊያጋልጡ ይችላሉ
- የብቸኛ መለያ ስርቆት ሂሳብዎን ለመጠበቅ የፋይናንስ ተቋማትዎን ወዲያውኑ ያነጋግሩ
- ጠንካራ የመክፈቻ ቃል/passphrases ይጠቀሙ እና ለብዙ ድረ-ገፆች ተመሳሳይ የመክፈቻ ቃል አይጠቀሙ
- የፀረ-ቫይረስ እና ፀረ-ማልዌር መተግበሪያዎች ወቅታዊ መሆኑን ያረጋግጡ
- እንደ አስፈላጊነቱ የስርዓት እና የሶፍትዌር ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግ
- ሁለት-ምክንያት እውነተኝነትን ተግባራዊ ማድረግ
- ጥሬ መረጃን በየጊዜው ማደስ
- የእርስዎን ሞባይል ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ይምረጡ
- የእርስዎን የሳይበር አስተማማኝ አስተሳሰብ እና ግንዛቤ ማዳበር
- ለበለጠ መረጃ በድረገጽ cyber.gov.au ይጎብኙ።